# “ትግል ለሀገር ትንሳኤ”

ጸሐፊ - ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ
አስተያየት - በላይ ገሠሠ

ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ በቅርቡ “ይኸውና ኤርትራ ሞተች፤ ትግል ለሀገር ትንሳኤ” በሚል ዓቢይ ባለ 55 ገፅ ጥናታዊ ዘገባ ማቅረባቸው ይታወሳል። ቀልቤን የሳበው በፅሑፉ የሰፈሩትን መሰረታዊ ጉዳዮችን በማንበቤ ብቻ አይደለም። በአርባ ዓመታት ውስጥ ከአንድ ኤርትራዊ ምሁር ይህን ዓይነቱ ሰበር አስተሳሰብ የያዘ ፅሑፍ በኢትዮጵያውያን መድረክ ላይ ሲቀርብ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑንም ጭምር ነው። የዛሬው አስተያየቴንም የሚያተኩረው በዚሁ ጥናታዊ ፅሑፍ ላይ ነው።




ፕሮፌሴር ተስፋፅዮን መድሃኔ ካሁን በፊት በርካታ መፃሕፍቶችን ለሕብረተሰቡ አበረክቷል። በየጊዜው በተለያዩ መድረኮች ብዙ ጥናታዊ ዘገባዎችን አቅርቧል። በተለያዩ ሚድያዎች ቀርበው በርካታ ቃለ ምልልሶችን አካሄዷል። ገና ከጥዋቱ የሻዕቢያና የህወሓት መሪዎች ፀረ ህዝብና ፀረ ሀገር ተግባርን በሃሳብ በመመከትና በማጋለጥ የአላማ የበላይነት ተቀዳጅተው የቆዩ ሰው ናቸው። ረዘም ላለ ጊዜም በውጭ በጀርመን ሀገር ውስጥ በብረመን ዩኒቨርሲቲ በማስተማርና በምርምር ስራ ላይ አሳልፏል። ባጠቃላይ ላለፉት አርባ ዓመታት ያህል ሳይታክቱ ለሰብኣዊ መብትና ክብር ተሟጓች በመሆን ሲሳተፉ መቆየታቸው የሰሩዋቸው ስራዎች ሁሉ ህያው ምስክሮች ናቸው።

ፕሮፌሴር ተስፋፅዮን መድሃኔን ከማደንቅላቸው ነገሮች አንዱ በትጥቅ ትግሉ ዘመን በተለይም ከመለስ ዜናዊ ጋር የነበራቸው የሃሳብ ግብግብ ነው። እሳቸው “የኤርትራ ትግል አበቃለት። በኢሳያስና በወያኔ እጅ ገብቷል። በእጅ አዙር ተጠልፏል። ከዛሬ ጀምሮ የኤርትራ ህዝብ ትግል አይደለም” በማለት በዚሁ ገፅ ከታች በስተግራ በኩል በእንግሊዝኛ የተፃፈውን መፅሐፍ የጠመንጃውን አፍ ሙዝ ወደታች ዘቅዝቀው ሲፅፉ፣ መለስ ዜናዊ ደግሞ በቁጭት ብድግ ብሎ በዚሁ ገፅ በስተቀኝ በኩል በትግርኛ ቋንቋ የተፃፈውን መፅሐፍ፣ ሽፋኑን በአማረኛ ሲተረጎም “የኤርትራ ህዝብ ትጥቅ ቁልቁል አይደፋም” በማለት የጠመንጃውን አፈ ሙዝ ወደ ላይ አንስቶ በማቆም በተቃራኒው እንደፃፈው የሚታወስ ነው።




“ላየኛው ከንፈር ለክርክር ታቸኛው ከንፈር ለምስክር” እንደተባለው ሁሉ፣ እነዚህ ግራና ቀኝ ያሉት ሁለት የታሪክ ገፅታዎችን የሚያሳዩ መፃሕፍቶች አሁን በእጄ ላይ ይገኛሉ። በመፅሐፉ ሽፋን ላይ እንደሚታየው ጠመንጃው የተቸከለበት ምድር ባልሳሳት መቃብር ይመስለኛል።



በመለስ ዜናዊ

በፕሮፌሴር ተስፋፅዮን በመለስ ዜናዊ ሰሞኑን በሚዲያ በኩል ያወጡትን ፅሑፍ “ይኸውና” በሚል የጀመሩበትን ምክንያት ከድሮ ጀምሮ ይሉት የነበሩትን ታሪካዊ ትስስር ያለው ይመስላል። ቀጥተኛ ትርጉሙም “ድሮም ደጋግሜ ብያችሁ ነበረ ይኸውና እንዳልኩት የኤርትራ ሞት ተረጋገጠ” የሚል መልእክት ያለው ነው የሚመስለኝ። ይሁን እንጂ አሁን ያቀረቡትን ጥናታዊ ፅሑፍ የኤርትራ ሞት መርዶ ነጋሪ ብቻ አይደለም። ሀገሪቱ ለሞት የዳረጓትን ዋና ዋና መንሲኤዎችንና ከወደቀችበት እንደገና የምትነሳበትን መፍትሄዎችንም ጭምር ቁልጭ አድርገው አስቀምጧል። እርግጥ ነው ላለፉት ሃምሳ ዓመታት በአካባቢው ለነበሩና በሂደቱ የተሳተፉ ሰዎች ይህንን ፅሑፍ ሲያነቡ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው ሁሉ መልሶ የሚያሳይ ፊልም ሆኖ እንደሚታያቸው አልጠራጠርም። በጉዳዩ ላልነበሩት አዲስ አንባቢዎች ደግሞ “ለካስ ይህም ነበረ” የሚያስብሉ፣ ለውይይትና ለክርክር የሚጋብዙ፣ (Provocative and sensitive political issues) ብዙ የተለያዩ ወቅታዊና ታሪካዊ ጉዳዮችን በጥናቱ ውስጥ አስፍሯል።

በተጨማሪም የጥናቱን አቀራረብ፣ ፍሬ ነገሩ፣ ታሪካዊ ትስስሩንና ይዘቱን ሲታይ ላለፉት አርባና ሃምሳ ዓመታት በአካባቢው የነበረውን ውጣ ውረድና ውስብስብ የፓለቲካ ጎዞ በዚሁ አጭር ፅሑፍ በጥንቃቄ ተቀርፆና ተቀነባብሮ መቅረቡ በጣም የሚደነቅ ነው። ጥናቱም እንዲሁ ለማወቅ ተብሎ ለተራ አንባቢዎች ብቻ የቀረበ ሳይሆን ለሌሎች ፃፊዎችና ተመራማሪዎችንም ጭምር እርሾ ሆኖ የሚያነሳሳ (inspirational) ነው። በሌላ አነጋገር ለፃሃፊዎችና ደራሲዎች እንደ ንድፈ ሃሳብ ሆኖ ሊያገለግልም የሚችል ነው።

ባጠቃላይ የፅሑፉን ቁልፍ ቁም ነገር የኤርትራን ትንሳኤ ማረጋገጥ ሲሆን በተጓዳኝ በብዙዎቻችን ዘንድ በአእምሮኣችን ውስጥ ሲጉላሉ የነበሩትን ጥርጣሪዎችና ጥያቄዎችም ጭምር በድፍረት ከተጠቀሱት ዓበይት ጎዳዮች ውስጥ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙባቿል። እነሱም

1. የኢሳያስና የህወሓት የረጀም ጊዜ ድብቅ አጀንዳ ምን እንደሆነ፣
2. የኤርትራን ትግል አቅጣጫውን እንዲስት በማድረግ በአቋራጭ የጠለፉት እነማን እንደሆኑ፣
3. የትግራይ ትግርኚን (የትግራይ ሪፓብሊክ) ፅንሰ ሐሳብ ተግባራዊ የማድረግ ዕቅድ ጋሃድ እየሆነ መምጣቱንና ዝግጅት መጀመሩን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች እንዳሉ
4. የተቃውሞ ጎራን ለማፍረስና ለማክሰም የ5ኛ ረድፍ ሚና በኤርትራና በኢትዮ • ያ
5. ኤርትራን እንደ ሀገር ለማፍረስ በደንከሊያና በአፋር አካባቢ እየተዶለተ ያለው ሚስጢር፣
6. ሁለቱን መንግስታት በስመ ተቃዋሚ የሚፈለፍሉዋቸውን ድርጅቶች የወደፊት ዕጣ ፋንታቸው፣
7. በኤርትራውያንና በኢትዮጵያውያን ሐቀኛ የዴሞራሲ ተጋዮች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ስትራተጂያዊ የትግል ዝምድና በሚመለከቱና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ሰፊ ሐተታ አቅርቧል።

ጥናቱን እንዳየሁት የኤርትራን ችግር ብቻ ለመፍታት ያነጣጠረ ፅሑፍ አይደለም። “በአፍሪቃ ቀንድ በተለይም በኢትዮ • ያና በኤርትራ መካከል ያለው መቋጫ ያጣ ችግር (chronic problem) ዋና መንሲኤው የኢሳያስና የህወሓት ስርዓቶች እንደሆኑ ይገልፃል። በመቀጠልም እነዚህ ምንትዬ የሰላም ፀሮች በቦታው እስካለሁ ድረስ ደግሞ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ከጅብ ምንጋጋ ለአንድ አፍታ እንኳን እፎይታ ያገኛሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ዘላቂና መሰረታዊ መፍትሄ ሊመጣ የሚችለው ደግሞ ከውጭ ሐይል ወይም ከራሳቸው ከችግር ፈጣሪዎች መንግስታትና መሪዎቸ አይደለም። እነሱ’ማ እኛን እርስ በርሳችን እያባሉ ለመኖር ዕቅድና ስትራተጂ ቀይሰው ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል ሲሰሩበትና ሲንቀሳቀሱበት ቆይቷል። ለወደፊትም ዕድል እስካገኙ ድረስ ለዘላለም ይቀጥላሉ። ነገር ግን “መድሃኒቱ ከባለቤቱ” እንደሚባለው ሁሉ ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት የሚቻለው የችግሩን ሰለባ የሆኑትን ህዝቦች በመተባበር በጋራ ጉዳይ ላይ የጋራ ትግል በማድረግ ብቻ ነው። ሌላ አማራጭ የለም። ስለዚህ የሀገርና የታሪክ ባለቤቶች ህዝቦች እንደሆኑ ሁሉ ታሪካቸውን ማደስና አሁን በአካባቢው ያለውን ገሃነማዊ የጨለማ አስተዳደር መለወጥ የሚችሉትም እነዚህ ሁለት ባለታሪክ ህዝቦች ብቻ ናቸው” በማለት ፃሃፊው በማያወላውል መንገድ ግልፅ አድርገው አስምረውበታል። እንዴት መተባበር እንደሚቻልም መፍትሄ ሃሳብም ጠቁሟል።

በማጠቃለል ለሁሉም ወገኖቼና ጓደኞቼ ለማስታወስ የምፈልገው ይህ ፅሑፍ የመጨረሻ ባይሆንም ጊዜውን ጠብቆ የመጣ በር ከፋች ፅሑፍ ነው። ፍንጭ አሳይቷል። መፍትሄዎችንም ጠቁሟል። ስለዚህ ይህ ፅሑፍ ሁላችንም እንድናነበውና እንደነዚህ የመሳሰሉት ጀግኖች ፀሐፊዎችንም አይዛችሁ!! በርቱ!! እኛም አለን ከጎናችሁ!! እንድንላቸው ሀገር ወዳድ ነን የምንል ሁሉ የሞራል ግዴታ አለብን። “ትንሽ ቃልም ብትሆን ታሪክ ታስመዘግባለች” እንደተባለው ሁሉ ፀሐፊው ለሁሉም ይበጃል ብለው ያቀረቡትን የመፍትሄ ሃሳብም በሚዲያ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር በመሬት ላይም የብዙዎች መወያያ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅብናል። ይህንን ለማመቻቸት ደግሞ ያለንን ማሕበራዊ ሚዲያዎች ተጠቅመን ሌሎቹንም እንዲያነቡት ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። ታስበቦት የተሰራ ስራ ነውና።

ሙሉዉን ለማንበብ እዚህ ይጫኑ http://www.ethiomedia.com/10parts/eritrea_tinsae.pdf